# የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን

# የ2014 በጀት አመት ዕቅድ

# (ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ለቦርድ የቀረበ)

ጥቅምት 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ማውጫ** **ገጽ**


1. መግቢያ ........ 2
1.1 ራዕይ ........ 2
1.2 ተልዕኮ ........ 3
1.3 እሴቶች ........ 3
1.4 የባለሥልጣኑ ስልጣንና ተግባራት ........ 3
2. የተቋሙ ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ........ 6
2.1. የውስጣዊ እና ውጪያዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ ለዕቅዱ እንደመነሻ ........ 7
2.1.1 ውስጣዊ ዳሰሳ (ጥንካሬ እና ድክመት) ........ 7
2.1.2 ውጪያዊ ዳሰሳ (መልካም አጋጣሚና ሥጋት) ........ 8
2.2. የተቋሙን የእስከአሁን አፈፃፀም ለዕቅዱ እንደመነሻ ........ 10
3. የ2014 በጀት አመት ዝርዝር ዕቅድ ........ 11
4. ዕቅዱን ለማሳካት ታሳቢ የተደረጉ ጉዳዮች/ ነጥቦች ........ 21
5. የክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማ እና ግብረ መልስ ሥርዓት ........ 21
6. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች እና የሚወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ........ 22
6.1 ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ........ 22
6.2 የሚወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ........ 23

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 1148/2011 በወጣ አዋጅ የኮሙኒኬሽን ዘርፍን እንዲቆጣጠር የተቋቋመ አዲስ የፌዴራል መንግስት መ/ቤት ነው።

የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው መሆናቸውን በመገንዘብ፣ መንግስት የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕደገት ለማሻሻል በውድድር ላይ የተመሠረተ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት እንዲኖር የወሰነ በመሆኑ እና በቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውድድርን ለማስፈን ያስቀመጠውን የፖሊሲ አቅጣጫ ለማሳካት ነፃ፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን መ/ቤት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

በዚሁ መሠረት ባለሥልጣን መ/ቤቱ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የፖስታ እና የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍን በመምራትና በመቆጣጠር ረገድ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ ለመወጣት እንዲሁም በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው መሠረት የቴሌኮሙኒኬሽን ሪፎርም ስራውን ለማሳካት አዲስ አለም አቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮችን ፈቃድ ሰጥቶ በማስገባት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በውድድር ላይ ተመስርቶ እንዲሰጥ ለማስቻል ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በመሆኑም የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን የተሰጠው ዓላማ በውጤታማነት ለማሳካት የ2014 በጀት አመት ዕቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

### 1.1 ራዕይ

የኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ እድገት እና ፈጠራን በማጎልበት ኢትዮጵያን ወደ ዓለም አቀፍ ዲጂታል ማህበረሰብ ማሸጋገር።

### 1.2 ተልዕኮ

በኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን ዘርፍን በግልጽነት እና በብቃት በመቆጣጠር እና በሁሉም  የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች ዘንድ ፍትሃዊ ተወዳዳሪነት መኖሩን በማረጋገጥ፣ ተደራሽነትን ማሳደግ፣ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መጠበቅ እና ከፍተኛ ጥራት ያለው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ ማስቻል።

### 1.3 እሴቶች

- ነጻነት/Independence/
- ታማኝነት/Integrity/
- ፈጠራን ማበረታታት/Innovation/
- ቀዳሚ ሆኖ መገኘት/Lead the Way/
- የህዝብ አገልጋይነት/Public Stewardship/
- በጎ ተጽዕኖ መፍጠር/Make an Impact/
- ሌሎችን ማስቀደም/Selfless Approach/
- ለሁሉም ስኬት መስራት/Caring for the Success of All/ ወዘተ

### 1.4 የባለሥልጣኑ ስልጣንና ተግባራት

ለኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 የተሰጡ ስልጣንና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡-

- የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመንግስት ፖሊሲ መሠረት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ ሊያበረክት በሚችል መልኩ መካሄዱን ያረጋግጣል፤
- የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

- በአዋጁ በተደነገጉ ባለሥልጣኑን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በሕዝብ ጥያቄ መሠረት ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ያደርጋል፤
- በአዋጁ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ ለማከናወን ከማንኛውም ባለፈቃድ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር፣ የፖስታ ኦፕሬተር ወይም ብሮድካስተር አስፈላጊ የሆነ መረጃ መጠየቅ ይችላል፤
- ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ኃላፊነት ከተሰጣቸው ተቋማት እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚሰጥበትን የቴክኒክ ደረጃ ይወስናል፤ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት የተወሰነለትን የጥራት ደረጃ ጠብቆ መሰጠቱን ይቆጣጠራል፤
- በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚጠየቀውን ታሪፍ ይቆጣጠራል፤
- የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ፈቃድ ያሻሽላል፣ ያድሳል፣ ያግዳል ወይም ይሰርዛል፤
- ከቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ጋር ተገናኝተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉ የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ዓይነት ይቆጣጠራል፤
- በኢትዮጵያ ውስጥ ለንግድ፣ ለመንግሥት፣ ለሃገር መከላከያ እና ለብሔራዊደህንነት ሥራዎች ጥቅምላይ የሚውሉ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀምን በተመለከተ ሚኒስቴሩን፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣንን እና በኢትዮጵያ የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በበላይነት ለመምራት ስልጣን የተሰጠው ተቋምን ጨምሮ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይፈቅዳል፣ ይቆጣጠራል፤
- በዓለም አቀፍ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ደንቦች መሠረት በኢትዮጵያ የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በበላይነት ለመምራት ስልጣን ከተሰጠው ተቋም ጋር በመመካከር ለሳተላይት ምህዋር ቦታ ምዝገባ ያመለክታል፣ ያሳውቃል፣ ያስተባብራል፤
- ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ፕላን ያዘጋጃል፣ ይመድባል፣ ያስተዳድራል፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

- የኢንተርኔት ፕሮቶኮል አድራሻና የሀገሪቱን የከፍተኛ ደረጃ ዶሜይን ጨምሮ የዶሜይን ስሞችን ይመድባል፣ ያስተዳድራል፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤
- በተለያዩ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጭዎች መካከልየሚኖረውን የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርኮች ኢንተርኮኔክሽን ይቆጣጠራል፤
- የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብት ያስጠብቃል፤
- በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኦፕሬተሮች መካከል እንዲሁም በተጠቃሚዎች እና በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኦፕሬተሮች መካከል የሚነሱ ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ አለመግባባቶችን ይፈታል፤
- አካል ጉዳተኞች እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚኖራቸውን ተደራሽነት የሚያግዙትን ጨምሮ አዳዲስ የኮሙኒኬሽን ቴክኒኮች እና ቴክኖሎጂዎችን ለማልማት እና ለመጠቀም የሚያስችሉ ምርምሮችን ያበረታታል፤
- የኮሙኒኬሽን አገልግሎት መስጠት እና ማካሄድን በተመለከተ በፖሊሲና የሕግ ጉዳዮች ላይ መንግሥትን ያማክራል፤
- ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር በመቀናጀት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሬጉላቶሪ ጉዳዮችን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ጉባዔዎች እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዘንድ ኢትዮጵያን ይወክላል፤ የኮሙኒኬሽን አገልግሎትን በተመለከተ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አተገባበር ይከታተላል፤ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀምን በተመለከተ ከአህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሠራል፤
- በቴሌኮሙኒኬሽን መስክ የሚሰጥ የቴክኒክ ትምህርት እንዲስፋፋ ከትምህርት ተቋማት ጋር ይተባበራል፤
- በአዋጁ ድንጋጌዎችና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የፈቃድ ክፍያዎችን፣ ከኦፕሬተር የሚሰበሰቡ ክፍያዎችን እና ሌሎች የሬጉላቶሪ ክፍያዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

- የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍን በተመለከተ ኢትዮጵያ የተቀበለችውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
- የአዋጁ ድንጋጌዎች፣ የፈቃድ ሁኔታዎች እና በአዋጁ መሠረት በባለስልጣኑ የወጡ መመሪያዎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ይመረምራል፣ ተፈጻሚነቱን ለማስከበር አስፈላጊ የሆኑ ውሳኔዎችን ይሰጣል፤
- የአዋጁን አፈጻጸም በሚመለከት በብሮድካስተሮች ላይ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች እና አለመግባባቶች ምላሽ ይሰጣል፣ ይፈታል፤
- የዩኒቨርሳል አክሰስ የፋይናንስ ድጋፍ ማቋቋም እና ማስተዳደርን ጨምሮ የዩኒቨርሳል አክሰስ ግብን ይወስናል፣
- የኢንፎርሜሽን ደህንነት፣ የመረጃ ግላዊነት እና ጥበቃን ያበረታታል፤
- ስለ ኤሌክትሮኒክ ፊርማ በሌላ ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አስተማማኝ እንዲሆን የኤሌክትሮኒክ ፊርማን ጥቅም ላይ በማዋል በማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚደረግ ግንኙነትን እውነተኛነት እና አስተማማኝነት ያረጋግጣል፤

## 2. የተቋሙ ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ

ተቋማት ተልዕኳቸውን የሚፈፅሙበት የሥራ ከባቢ በውስጣዊ እና በውጫዊ የለውጥ ግፊቶች የተነሳ አዎንታዊ እና አሉታዊ ተፅኖዎች የሚፈራረቁበት እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡ ይሁንና ተቋሙ በአዲስ መልክ ተዋቅሮ ወደ ስራ የገባ ቢሆንም ያለውን ውስጣዊና እና ውጫዊ ሁኔታዎች እንደሚከተለው ለማየት ተሞክሯል፡፡

## 2.1. የውስጣዊ እና ውጪያዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ ለዕቅዱ እንደመነሻ

### 2.1.1 ውስጣዊ ዳሰሳ (ጥንካሬ እና ድክመት)

የተቋሙ ውስጣዊ ጥንካሬና ድክመት ዳሰሳ በሰው ኃብት ሁኔታ፣ በሥራ አካባቢ እና በአሠራር ሥርዓቶች አኳያ በመተንተን ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

❖ **ጥንካሬ**

- በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት መሰረት አድርጎ ስራ ለማስጀመር የሚያስችል መዋቅር ዘርግቶ ወደ ስራ መግባቱ፣
- ተቋሙን በግብዓት (በሰው ኃይል፣ በበጀት፣ በማቴሪያል፣ ወዘተ…) ለማደራጀት ያለ ተነሳሽነት፣
- ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም፣ በዘርፉ ላይ የረጅም ጊዜ ልምድ፣ ተመክሮ እና ክህሎት ያላቸው ሠራተኞች መኖር፣
- የኮሙኒኬሽን ዘርፉን ለመምራት እና ለማስተዳደር እንዲሁም ተልዕኮውን ለማሳካት የሚያግዙ የህግ ማዕቀፍ መኖሩ፣
- የለጋሽ ድርጅቶች ተቋሙን ለመደገፍ ያላቸው ተነሳሽነት መኖር ለአብነት፡- ከወርልድ ባንክ የተገኘ የገንዘብ ድጋፍ መኖር
- የሰራተኛውን አቅም በስልጠና ለማጎልበት የፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግ ከዓለም አቀፍ ድርጆቶች በኩል ፍላጎት መኖር፣

❖ **ድክመት**

- ስትራቴጂክ ዕቅድ አለመኖር፣
- ተቋሙን በበቂ ደራጃ በግብዓት (በሰው ኃይል፣ በበጀት፣ በተሽከርካሪ፣ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ… ወዘተ) አለመሟላቱ፣
- የህግ ማእቀፎች በተሟላ ደረጃ ተዘጋጅቶ/ተሻሽሎ ስራ ላይ አለመዋል፣
- ከመንግሥት ከሚመደብለት በተጨማሪ ከራሱ ገቢ በጀት በመመደብ መጠቀም አለመቻል፣

- በሌሎች ሀገራት ከሚገኙ አቻ ተቋማት ጋር በበቂ ደረጃ የልምድ ልውውጥ እና ምርጥ ተሞክሮዎችን መቅሰም አለመቻል፣
- ሠራተኛውን ለማብቃት በቂ የአቅም ግንባታ ስልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች አለመከናወኑ፣
- ምቹ የስራ አካባቢ አለመፍጠር ለአብነት፡- ለስራ ምቹ የሆነ ቢሮ አለመኖር፣ የሰራተኞች የካፍቴሪያ አገልግሎት አለመኖር፣

## 2.1.2 ውጪያዊ ዳሰሳ (መልካም አጋጣሚና ሥጋት)

የተቋሙ መልካም አጋጣሚና ሥጋት ዳሰሳ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በቴክኖሎጂ እና በህጋዊ ሁኔታ በመተንተን ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

❖ **መልካም አጋጣሚ**

- ባለሥልጣኑ ነፃ፣ ገለልተኛ እና ተጠያቂነት ለጠቅላይ ሚኒስተሩ የሆነ ተቆጣጣሪ መ/ቤት ሆኖ መቋቋም፣
- የኮሙኒኬሽን ዘርፍን ለመደገፍ የመንግስት ቁርጠኝነት መኖር፣
- በመንግስት የዲጅታል ስትራቴጂ መዘጋጀቱ፣
- የቴሌኮሙኒክሽን ዘርፍ ሊበራላይዝ መደረጉ የዘርፉን እድገት ለማፋጠን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመት ለመሳብ፣ ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ የሚያመጣ እና የስራ እድል እንዲፈጠር ያስችላል፤
- ዓለም ባልተጠበቀ ፍጥነት አራተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት እያካሄደች መገኘቷ፤
- የኮሙኒኬሽን ኢንዱስትሪው በፍጥነት እያደገ መሄድ፤
- በተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች መካከል በሚፈጠረው የገበያ ውድድር ምክንያት የአገልግሎት ጥራት እንዲጨምር ያግዛል፤

- ስጋቶች

- የሀገሪቱ ሰላም የተረጋጋ አለመሆኑ፤
- የኮቪድ-19 ወረርሺኝ የዓለም ስጋት ሆኖ መቀጠሉ፣
- የዋጋ ግሽበት እየጨመረ መምጣቱ፤
- የውጭ ምንዛሪ እጥረት መኖሩ፤
- ዘርፉ የሚጠይቀውን ክህሎትና የስራ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች በገበያ ላይ ካለው ክፍያ አንፃር ተወዳድሮ በቅጥር ለማሟላት የሚያስችል ደመወዝና ጥቅማጥቅም አለመኖር፣
- ዕቅድን ለማስፈጸም የሚያስችል የበጀት ውስንነት፤
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ያለውን የሰው ኃይል ለማቆትም ሆነ ከገበያ ላይ በቂ ልምድና ክህሎት ያለው ባለሙያ ለመቅጠር እንዲያስችለው የተጠናው የደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም እስኬል ጥናት በበላይ አካል አለመፅደቅ፣
- ዲጂታል ከባቢ እና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የበለጸገ ኅብረተሰብን ለመገንባት የሚያስችላትን አቅም ገና አለመፈጠሩ፣
- ተጠቃሚዎች በኮሙኒኬሽን አገልግሎት መብት እና ግዴታ ላይ በቂ እውቀትና ትምህርት አለመኖሩ፣
- አዳዲስ የሚገቡ የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪዎች ከፍተኛ ልምድ ያላቸው በመሆኑ በተቆጣጣሪው ላይ ክፍተቶችን በመጠቀም ጫና የማሳዳር እድል ይኖራቸዋል፣
- ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚውሉ የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ውስንነት፤
- የዲጂታል ዲቫይድ (በፆታ፣ በአካባቢ፣ በኢኮኖሚ) መጠን ከፍተኛ መሆን፤
- በቴሌኮምና ተጓዳኝ የመገናኛ መሳሪያዎችና አገልግሎት ላይ የተጠቃሚዎች ግንዛቤ ማነስ፣
- የተጠቃሚዎች የደህንነት ስጋት መኖሩ፣
- የአገልግሎቶች ቅልጥፍና እና ጥራት መጓደል መኖር፣

- ቴክኖሎጂው በፈጣን ሁኔታ ተለዋዋጭ በመሆኑ የመጠቀሚያ መሳሪያዎች outdate በመሆን ድጋፍ ማግኘት አለመቻል፣
- የሳይበር ወንጀል እየተሰፋፋ መምጣት /cyber attack/፤

## 2.2. የተቋሙን የእስከአሁን አፈፃፀም ለእቅዱ እንደመነሻ

ባለስልጣኑ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በተደራጀ አግባብ ለመወጣት የሚያስችለው የአሰራ ስርዓት የመዘርጋት ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም አንድ ደንብ (የቴሌኮሙኒኬሽን ሁሉን አቀፍ ተደራሽነት ፈንድ) ተዘጋጅቷል፡፡ 14 መመሪያዎች (የቴሌኮሙኒኬሽን ፈቃድ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥራት፣ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ታሪፍ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ተጠቃሚዎች መብት እና ጥበቃ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውድድር፣ የቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን፣ የኢንተርኮኔክሽን፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ማዛወር፣ የሲም ካርድ ምዝገባ፣ የሀገር ውስጥ ሮሚንግ አገልግሎት፣ መሬትንና ሕንፃን ለቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተልማቶች ዝርጋታ ስለመጠቀም፣ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ እና የክርክር አፈታት) ተዘጋጅቷል፡፡ 2 ስታንደርዶች (የቴሌኮሙኒኬሽን ሁሉን አቀፍ ተደራሽነት እና አገልግሎት ማዕቀፍ እና ብሔራዊ የፍሪኩዌንሲ ድልድል ዕቅድ) ተዘጋጅቷል፡፡ በድምሩ 17 የህግ ማዕቀፎችን የማዘጋጀት ስራ ሲሰራ 9ኙ የህግ ማዕቀፎች ፀድቀው ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ ቀሪ 5 የህግ ማዕቀፎች ከባለድርሻ አካላት የተገኙ ግብዓቶችን በማካተት ሰነዶቹን በማዳበር የመጨረሻ ረቂቅ የህግ ማዕቀፎች የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡

ለተለያዩ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ፈቃድ ከመስጠት እና ከማደስ አኳያ ለ119 የኢንተርኔት ካፌ እና ቴሌሴንተር ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን 393 ፈቃዶች ደግሞ ታድሷል፡፡ ለ142 የTVRO ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን 21 ፈቃዶች ደግሞ ታድሷል፡፡ ለ37 የውስጥና የውጭ ኬብል፣ የማዞሪያ እና የተርሚናል ዕቃዎች ተከላና ጥገና ሥራ ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን 105 ፈቃዶች ደግሞ ታድሷል፡፡ ለ392 የቫልዩ አድድ አገልግሎት (VAS) ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን 194 ፈቃዶች ደግሞ

ታድሷል። በአጠቃላይ ለ690 የተለያዩ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃዶች የተሰጡ ሲሆን 713 ፈቃዶች ደግሞ ታድሷል።

ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች የፍሪኩዌንሲ ፈቃድ ከመስጠት እና ከማደስ አንፃር ለ32 የፍሪኩዌንሲ ፈቃዶች የተሰጡ ሲሆን ለ54 ፍሪኩዌንሲ ፈቃዶች ታድሷል። ለ4 የVSAT መሣሪያዎች ፈቃድ ተሰጠ ሲሆን ለ19 የVSAT መሣሪያዎች ፈቃዶች ታድሷል። ለ242 የመገናኛ ሬዲዮ ፈቃዶች ተሰጥቷል።

ለፖስታ አገልግሎት ፈቃድ መስጠትና ማደስ አኳያ ለ16 የፈጣን መልዕክት አገልግሎት ፈቃዶች የተሰጡ ሲሆን 17 ፈቃዶች ደግሞ ታድሷል። እንዲሁም ለ1,908 የተለያዩ አይነት የቴሌኮሙኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷል። በዋናነትም ለአንድ የቴሌኮም ኦፕሬተር ፍቃድ ተሰጥቷል። ከተሰጡ አገልግሎቶች ማለትም ከፈቃድ መስጠት፣ ከፍቃድ ዕድሳት እና ከቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት እንዲሁም ከፍሪኩዌንሲ ክፍያዎች ብር 53,916,058.48 ገቢ መሰብሰብ ተችሏል።

### 3. የ2014 በጀት አመት ዝርዝር ዕቅድ

#### I. የተገልጋይ እይታ (25%)

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 1. የአገልግሎት ቅልጥፍና እና ውጤታማነት ማሻሻል**

**ግብ 1. 2,703 የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የአዲስ ፈቃድ እና ዕድሳት ተገልጋዮች ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት ማግኘታቸው ይረጋገጣል።**

ተግባር 1. 80 አዲስ የውስጥና የውጭ የቴሌኮሙኒኬሽን መገልገያዎች ተከላና ጥገና ስራዎች ፈቃድ መስጠት እና 100 ውስጥና የውጭ የቴሌኮሙኒኬሽን መገልገያዎች ተከላና ጥገና ስራዎች ፈቃዶችን ማደስ፣

ተግባር 2. 870 የቫልዩ አድድ አገልግሎት ፈቃድ መስጠት እና 600 የቫልዩ አድድ አገልግሎት ፈቃዶችን ማደስ፣

ተግባር 3. ለ1000 የመገናኛ ሬዲዮ መሳሪያዎች አዲስ ፈቃድ መስጠት፣

ተግባር 4. 12 የቪሳትና ሌሎች የሳተላይት መቀበያና ማሰራጫ መሳሪያዎች ፈቃድ መስጠት እና 40 ፈቃዶችን ማደስ፣

ተግባር 5. ለአንድ ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ፈቃድ መስጠት፣

**ግብ 2. 82 የፖስታ አገልግሎት የአዲስ ፈቃድ እና ዕድሳት ተገልጋዮች ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት ማግኘታቸው ይረጋገጣል፡፡**

ተግባር 1. 30 የግል ፈጣን ፖስታ አገልግሎት ፈቃድ መስጠት እና 52 ፈቃዶችን ማደስ)፣

**ግብ 3. 310 የፍሪኩዌንሲ አዲስ ፈቃድ እና ዕድሳት ተገልጋዮች ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት ማግኘታቸው ይረጋገጣል፡፡**

ተግባር 1. 100 አዲስ የፍሪኩዌንሲ ፈቃድ መስጠት እና 210 የፍሪኩዌንሲ ፈቃድ ማደስ፣

**ግብ 4. 3960 የቴሌኮሙኒኬሽን መገልገያ መሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት ተገልጋዮች ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት ማግኘታቸው ይረጋገጣል፡፡**

ተግባር 1. በሀገር ውስጥ የሚገጣጠሙ እና ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ 3960 የተለያዩ አይነትና ሞዴል ያላቸው የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎችን የቴክኒክ መስፈርት በመፈተሽ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ መስጠት፣

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 2. የተገልጋዮችን ግንዛቤ ማሳደግ**

**ግብ 5. 13 ልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎችንና መድረኮችን በመጠቀም የኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሬጉላቶሪ ስራዎችን በተመለከተ የተጠቃሚዎች ግንዛቤ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች መብትና ግዴታዎችን አስመልክቶ 6 ማስታወቂያዎች በማዘጋጀት በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች አየር ላይ እንዲውል ማድረግ፣

ተግባር 2. በተጠቃሚዎች መብት ጥበቃ፣ በመሰረተ ልማት ደህንነት እና በአገልግሎት ሰጪዎች የሥነ ምግባር (Code of Conduct) ግንባታ ላይ 3 የግንዛቤ ማስጨበጫ የምክክር መድረኮች ማካሄድ፣

ተግባር 3. ሁለት የቴሌቭዥን እና ሁለት የሬዲዮ ፕሮግራሞች በማዘጋጀት የባለስልጣኑን ተግባርና ኃላፊነት ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 3. የተጠቃሚዎች መብት እና ጥበቃን ማጠናከር**

**ግብ 6. በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኦፕሬተሮች መካከል የሚነሱ ቅሬታዎችን በመመርመር አለመግባባቶችን የመዳኘት እና የመፍታት ስርዓት እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች የሚያቀርቡትን ቅሬታ ወይም አቤቱታ መቀበል፣ መመርመር እና ውሳኔ መስጠት፣

**ግብ 7. በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች እና በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኦፕሬተሮች መካከል የሚኖሩ ቅሬታዎችን በመመርመር አለመግባባቶችን የመዳኘት እና የመፍታት ስርዓት እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1. የኮሙኒኬሽዕን አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚያቀርቡትን ቅሬታ ወይም አቤቱታ መቀበል፣ መመርመር እና ውሳኔ መስጠት፣

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 4. የተገልጋዮችን እርካታ ማሳደግ**

**ግብ 8. የተገልጋዮችን የእርካታ ደረጃ ለማወቅ የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1.እርካታ ዳሰሳ ጥናት ቢጋር (TOR) ማዘጋጀት፣

ተግባር 2. ልዩ ልዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች በመጠቀም እርካታ ደረጃ መረጃ መሰብሰብ፣

ተግባር 3. የተገኙትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ የእርካታ ደረጃን መተንተን፣

ተግባር 4. ረቂቅ የእርካታ ዳሰሳ የጥናት ሰነድ ማዘጋጀት፣

ተግባር 5. ረቂቅ የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ሰነዱን ለማኔጅመንት በማቅረብ ግብአት በማሰባሰብ ማዳበር፣

ተግባር 6. የመጨረሻ የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ሰነድ ማዘጋጀት፣

**II. የፋይናንስ እይታ (15%)**

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 5. ገቢን ማሳደግ**

**ግብ 9. የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ እና የሬጉላቶሪ አገልግሎቶች ገቢ በወቅቱ እና በአግባቡ እንዲሰበሰብ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1. ከፍሪኩዌንሲ ፈቃድ እና የፈቃድ ዕድሳት 36 ሚሊዮን ብር መሰብሰብ፣

ተግባር 2. ከብቃት ማረጋገጫ የአገልግሎት ክፍያ ብር 250 ሺህ ብር መሰብሰብ፣

ተግባር 3. ከቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች፣ ከመገናኛ ሬዲዮ፣ ከሳተላይት መቀበያና ማሰራጫ መሣሪያዎች እና ከግል ፈጣን ፖስታ አገልግሎት አዲስ ፈቃድ መስጠትና ዕድሳት አገልግሎት ክፍያ ብር 130 ሚሊዮን ብር መሰብሰብ፣

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 6. የበጀት አጠቃቀም ማሻሻል**

**ግብ-10. የበጀት አጠቃቀም ወደ 90% በላይ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1. የተቋሙን የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት በማሰባሰብ በየወሩ የበጀት ጥያቄ ማቅረብ፣ የበጀት ዝውውር ጥያቄ አዘጋጅቶ ማቅረብ እና ልዩ ልዮ ክፍያዎችን በወቅቱ መፈፀም፥

ተግባር 2. የተቋሙን የ2014 የፕሮግራም በጀት የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት፣ የዘጠኝ ወርና ዓመታዊ የበጀት አጠቃቀም መገምገም እና ወቅታዊ ሪፖርት ማዘጋጀት፣

ተግባር 3. የተቋሙን የ2015 ፕሮግራም በጀት ዕቅድ ማዘጋጀት፣

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 7. የሀብት አጠቃቀም እና አስተዳደር ሥርዓትን ማጎልበት**

**ግብ 11. ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት በዕቅድ የተመራ ግዥ መፈጸሙ እና ውጤታማ የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም መኖሩ ይረጋገጣል፡፡**

ተግባር 1. የተቋሙን ስትራቴጂያዊ እና ኦፕሬሽናል ዕቅድ ማዘጋጀት እና አፈጻጸሙን በየወቅቱ መገምገም፣

ተግባር 2. በጀት እና ንብረት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን በውስጥ ኦዲት ስራ ማረጋገጥ፣

ተግባር 3. በዕቅድ የተመራ ግዥ መፈጸም፣

ተግባር 4. በመንግስት መመሪያ መሠረት የተተገበረ የንብረት አስተዳደር መኖሩን ማረጋገጥ፣

ተግባር 5. በቅጥር፣ በዕድገት፣ በዝውውር እና በምደባ የሰው ኃይል መሟላቱን ማረጋገጥ፣

**III. የውስጥ አሰራር እይታ (50%)**

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 8. የቁጥጥር እና የህግ ማስፈጸም ስራዎችን ማሻሻል**

**ግብ 12. የፍሪኩዌንሲ አስተዳደር እና ሞኒተሪንግ ስራዎችን በማጠናከር ከህገወጥ የፍሪኩዌንሲ አጠቃቀም እና ከኢንተርፌራንስ ነጻ የሆነ የፍሪኩዌንሲ አጠቃቀም መኖሩ ይረጋገጣል።**

ተግባር 1. 40 የፍሪኩዌንሲ ሞኒተሪንግ ስራዎች ማከናወን፣

ተግባር 2. 24 በአለምአቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ህብረት የሬዲዮ ኮሙኒኬሽን ቢሮ የሚታተሙ አለምአቀፍ የፍሪኩዌንሲ መረጃ ሰርኩላር (BR IFIC) መገምገም እና የኮኦርዲኔሽን ስረዎችን ማከናወን፣

**ግብ 13. የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥራት ቁጥጥር እና ኢንስፔክሽን ስራዎችን በማጠናከር የአገልግሎት ጥራት ስታንዳርድ መስፈርቶች መሟላታቸው ይረጋገጣል።**

ተግባር 1. የቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ የህግና የቁጥጥር ማዕቀፎች አተገባበር ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣

ተግባር 2. የድራይቭ ቴስት መሣሪያን በመጠቀም በሞባይል ኔትዎርክ ላይ የአገልግሎት ጥራት ቁጥጥር ማከናወን፣

ተግባር 3. በየሩብ ዓመቱ ከብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የሚቀርቡ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥራት ሪፖርቶችን መገምገም፣

ተግባር 4. የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባለፈቃዶች የፈቃድ ሁኔታዎችን አሟልተው እና አክብረው መስራታቸውን ለማረጋገጥ የኢንስፔክሽን ሥራ መስራት፣

**ግብ 14. የፖስታ አገልግሎት ጥራት ቁጥጥር እና የኢንስፔክሽን ስራዎችን በማጠናከር የመልዕክት ፍጥነት እና ደህንነት ስንታንዳርድ መስፈርቶች መሟላታቸው ይረጋገጣል፡፡**

ተግባር 1. በየሩብ ዓመቱ ከብሔራዊ የፖስታ አገልግሎት ሰጪ የሚቀርቡ የፖስታ አገልግሎት ጥራት ሪፖርቶችን መገምገም፣

ተግባር 2. የፖስታ አገልግሎት ባለፈቃዶች የፈቃድ ሁኔታዎችን አሟልተው እና አክብረው መስራታቸውን ለማረጋገጥ በአዲስ አበባ እና በክልል ከተሞች የኢንስፔክሽን ሥራ መስራት፣

ተግባር 3. የፖስታ አገልግሎት ዘርፍ የህግና የቁጥጥር ማዕቀፎች አተገባበር ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 9. ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶች ትግበራን ማሳደግ**

**ግብ 15. ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶች ትግበራን ለማሳደግ የመረጃ ስርዓት ይዘረጋል፣ የዳታ ማዕከል ይቋቋማል፡፡**

ተግባር 1. የተቋሙን የሲስተም አጠቃቀም እና ደህንነት ማኑዋል ማዘጋጀት፣

ተግባር 2. የተቋሙን የተቀናጀ የመረጃ ሥርዓት ፍላጎት ጥናት ማድረግ፣

ተግባር 3. የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥሮችን ለመመደብ፣ ለማስተዳደር እና በዳታ ቤዝ መዝግቦ ለመያዝ የሚስችል ስርዓት (Numbering Management System) መዘርጋት፣

ተግባር 4. የዳታ ማዕከል ማቋቋምና ማደራጀት፣

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 10. የኢንተርኔት ሀብት አስተዳደር እና የመሰረተ ልማት ደህንነት ማጎልበት**

**ግብ 16. የኢንተርኔት ሀብት አስተዳደር እና የመሰረተ ልማት ደህንነት ለማጎልበት 3 ጥናቶች ይደረጋሉ።**

ተግባር 1. የዶሜይን ስምና የአይፒ አድራሻ አጠቃቀምና አስተዳደር ጥናት ማድረግ፣

ተግባር 2. የመንግስት ሠርቲፊኬሽን ባለስልጣን ማቋቋም ጥናት ማድረግ፣

ተግባር 3. የኤሌክትሮኒክ ንግድ ሥርዓት ትግበራ እና ቁጥጥር ጥናት ማድረግ፣

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 11. የህግና የቁጥጥር ማዕቀፎች ዝግጅት ማሻሻል**

**ግብ 17. 2 አዋጆች፣ 1 ደንብ፣ 4 መመሪያዎች፣ 4 የቴክኒክ ስታንዳርዶች እና ጋይድላይኖች እንዲሻሻሉና እንዲዘጋጁ ይደረጋል።**

ተግባር 1. የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ እና የልዩ ልዩ የሬጉላቶሪ አገልግሎቶች ክፍያ መመሪያ ማዘጋጀት፣

ተግባር 2. መሬትና ህንጻን ለቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተልማት ስለመጠቀም መመሪያ ማዘጋጀት፣

ተግባር 3. የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ መመሪያ ማዘጋጀት፣

ተግባር 4. የዶት ኢት ዶሜይን ስም አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ማዘጋጀት፣

ተግባር 5. የፈቃድ መስፈርቶች ጋይድላይን ማዘጋጀት፣

ተግባር 6. የአጭር ርቀት ገመድ አልባ መሣሪያዎች ስታንዳርድ/የቴክኒክ መስፈርት) ማዘጋጀት፣

ተግባር 7. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ማስፈፀሚያ ደንብ ማዘጋጀት፣

ተግባር 8. የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል አዋጅ ማሻሻል፣

ተግባር 9. የፖስት አገልግሎት አዋጅ ማሻሻል፣

ተግባር 10. ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥሮች ፕላን ማዘጋጀት፣

ተግባር 11. የሞባይል ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥራት ለመለካት የሚረዳ ዘዴና ማኑዋል (Developing Telecommunication Quality of Services Measurement Methodology and Guideline) ማዘጋጀት፣

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 12. የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት እና የአገልግሎት አቅርቦትን ማሳደግ፡፡**

**ግብ 18. የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት እና የአገልግሎት አቅርቦትን ለማሳደግ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የአሰራር ማኑዋል እና የፕሮጀክት ግምገማና ክትትል ጋይድላይን እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1. የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት እና አገልግሎት ፈንድ ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት፣

ተግባር 2. የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት እና አገልግሎት ፈንድ የአሰራር ማኑዋል እና ስርዓት ማዘጋጀት፣

ተግባር 3. የሁሉን አቀፍ ተደራሽነት እና አገልግሎት ፈንድ የፕሮጀክት ክትትል እና ግምገማ ጋይድላይን ማዘጋጀት፣

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 13. የውድድር እና የገበያ ጥናት ሥርዓት ማጠናከር**

**ግብ-19. የውድድር እና የገበያ ጥናት ሥርዓት ለማጠናከር የታሪፍ እና የጉልህ ገበያ ድርሻ ልየታ ጥናቶች ይደረጋሉ፡፡**

ተግባር 1. የኢንተርኮኔክሽን፣ የመሰረተ ልማት መጋራት፣ የሞባይልና መደበኛ ጥሪ ልውውጥ እና የሀገር ውስጥ ሮሚንግ ክፍያ ዋጋ ጥናት ማካሄድ፣

ተግባር 2. የቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ዳሰሳ ጥናት እና ጉልህ የገበያ ድርሻ ልየታ ጥናት ማካሄድ፣

**IV. የተቋማዊ መማማር እና እድገት እይታ (10%)**

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 14. የሰራተኞችን እርካታ ማሳደግ**

**ግብ 20. ምቹ የስራ አካባቢ እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1. የቢሮ አቀማመጥ ማሻሻል እና አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች እንዲሟሉ ማድረግ፣

ተግባር 2. ሰራተኞች የሚያነሷቸውን ቅሬታዎች በወቅቱ መፍታት፣

ተግባር 3. የተቋሙ ሰራተኞች እርካታ ያለበትን ደረጃ ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት ማድረግ፣

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 15. የሰራተኞችን ብቃት ማጎልበት**

**ግብ 21. የአቅም ክፍተትን መሰረት በማድረግ 80 ባለሙያዎች በ10 የስልጠና አይነቶች ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1. 80 ባለሙያዎችን በ10 የስልጠና አይነቶች ማሰልጠን፣

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ 16. የአመራር ብቃት ማጎልበት**

**ግብ 22. የአቅም ክፍተትን መሰረት በማድረግ 16 አመራሮች በ4 የስልጠና አይነቶች ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1. 16 አመራሮችን በ4 የስልጠና አይነቶች ማሰልጠን፣

## 4. ዕቅዱን ለማሳካት ታሳቢ የተደረጉ ጉዳዮች/ ነጥቦች

ይህን እቅድ በተሳካ ሁኔታ ለመተግበር ከዚህ በታች የተገለፁትን ታሳቢ አድርጓል፦

- ለዘርፉ በመንግስት የተሰጠው ትኩረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ይጠበቃል፤
- ለሥራ አስፈላጊ ግብአቶች (የሰው ኃይል፣ የበጀት፣ የአማካሪዎች፣ የተሽከርካሪ ወዘተ) በሚፈለገው መጠንና ጊዜ እንዲሟላ ይደረጋል፤
- የአለም አቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ እና ተሳትፎ የበለጠ እንደሚጎለብት ታሳቢ ተደርጓል፤
- በዝግጅት ላይ ያሉ የተለያዩ መመሪያዎች (የፍሪኩዌንሲ ክፍያ እና ስፔክትረም አጠቃቀም ደንብና መመሪያ፣ ወዘተ) ተጠናቀውና ፀድቀው ስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፤
- ለአመራሮች እና ባለሙያች ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ስልጠናዎች እና የሌሎች አገሮች ልምድ እንደያገኙ ይደረጋል፤
- ሥራ ቆጥሮ የመስጠትና የመቀበል ባህል እንዲዳብር ይደረጋል፣ውጤትን መሰረት ያደረገ የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 5. የክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማ እና ግብረ መልስ ሥርዓት

- ሠራተኛው አፈፃጸሙን እንዲያሻሽል የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ማድረግና በአፈፃፀም ልቀው የተገኙትን በምዘና ዕውቅና የሚሰጥት አሰራር ተግባራዊ ይሆናል፤
- በዕቅድ በተቀመጡ ዝርዝር ስራዎች አፈፃፀም ላይ ያተኮረ ወጥነት ያለው የክትትል እቅድ በማዘጋጀት የሥራ ክትትል በየደረጃው ይደረጋል፤
- በእቅዱ ላይ የተቀመጡትን ግቦችና ተግባራት አፈፃፀም መሠረት ያደረገ የአፈፃፀም ሪፖርት በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ፣ በግማሽ ዓመትና በየዓመቱ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፤

- የዕቅዶችን አፈፃፀም ውጤት፣ ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው፣ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት ለተሻለ ቀጣይ አፈፃፀም ድጋፍ ይደረጋል፤
- የመስክ ግምገማዎችና የሱፐርቪዥን ስራዎችን በተቀናጀ መልኩ በማካሄድ ለውሳኔ የሚያግዙ መረጃዎችን ማሰባሰብና በአግባቡ እንዲተነተን ይደረጋል፤
- የባለስልጣኑ አጠቃላይ ግምገማ በሩብ ዓመቱ፣ በ6 ወር፣ በዘጠኝ ወርና በዓመቱ መጨረሻ ላይ ይደረጋል፤
- በሚደረጉ ግምገማዎች የሚለዩ ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸው ልምዶች እንዲቀመሩና እንዲስፋፉ ይደረጋል፤
- የግምገማ ውጤትን መሰረት በማድረግ የግብረ-መልስ ሪፖርት ይዘጋጃል፡፡

# 6. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች እና የሚወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

## 6.1. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

- ከደሞወዝና ጥቅማ ጥቅም አናሳ መሆን ጋር ተያይዞ የሰው ኃይል ፍልሰት እንዲሁም አዲስ የሰው ኃይል ቅጥር መፈፀም ያለመቻል፣
- የበጀት እጥረት፣
- የግዥ መጓተት በተለይም በማዕቀፍ ግዥዎች ምክንያት ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች በወቅቱ ተደራሽ ያለመሆን፣
- ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ የተሽከርካሪ እጥረት፣
- የተዘጋጁና የተሻሻሉ የህግ ማዕቀፎች በሚመለከተው አካል በወቅቱ ያለመፅደቅ፣

## 6.2. የሚወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

- በተለያዩ የቅጥር አግባቦች በመጠቀም የሰው ኃይል የሚሟላበት ዘዴ ይፈለጋል፣
- የበጀት እጥረቱን ለመቅረፍ ተቋሙ አዲስ በመሆኑ በግብአትና በሰው ኃይል የማደራጀት ስራ በሂደት ላይ መሆኑን ለገንዘብ ሚኒስቴር ግንዛቤ በማስጨበጭ ተጨማሪ በጀት እና ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ ተሽከርካሪዎች እንዲፈቀድ ጥረት ይደረጋል፣
- ከግዥ ኤጀንሲ ጋር በቅንጅት በመስራት የግዥ ሒደቱ እንዲሳለጥ ይደረጋል፣
- የተዘጋጁና የተሻሻሉ የህግ ማዕቀፎች በሚመለከተው አካል በተለይም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲፀድቁ ያለሰለሰ ጥረት ይደረጋል፡፡